# በደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/መንግስት አቅም ግንባታ ሴክተር 2002 ዓ.ም የግማሽ ዓመት አፈጻጸም ሪፖርት

ታህሳስ 2002 ዓ.ም
ሀዋሣ

1. **መግቢያ**.....................................................................................1
2. የሲቪል ሰርቪስ ማሻሻያ ኘሮግራም (CSRP) ....................................2
3. ያልተማከለ የወረዳ አስ/እና የመልካም አስ/ፓኬጅ.................................11
4. ፍትህ ሥርዓት ማሻሻያ ኘሮግራም (JSRP).......................................12
5. የምህንድስና አቅም ግንባታ ኘሮግራም (Ecbp) ...................................14
6. የኢንፎርሜሽን ኮሙንኬስን ------------------------------------------18
7. ያጋጣሙ ችግሮች.........................................................................29
8. በቀጣይ ግማሽ ዓመት የትኩረት ነጥቦች...............................................30

## መግቢያ

የአቅም ግንባታ ሴክተር የክልሉ ሕዝብ ከሚገኝበት ኋላ ቀርነትና ድህነት እንዲላቀቅና የተመዘገቡ የልማት ውጤቶች ቀጣይነት እንዲኖራቸው የማስፈፀም አቅም ችግሮችን ለመፍታት የሚያስችሉ ቁልፍ የትኩረት መስኮችን በመለየት ግብ ነድፈፎ በተግባር እንቅስቃሴ ላይ ይገኛል፡፡ የ2002 ዓ.ም ቁልፍ የትኩረት መስክ መሰረት ተቋማዊ የማስፈፀም አቅም የመገንባት ሥራ ትኩረት በመስጠት መሰረታዊ የስራ ሂደት ለውጥን በመተግበር ተቋማዊ ለውጥ የማምጣት ጉዳይ ትኩረት በማድረግ ውጤት በማስመዝገብ ላይ ይገኛል፡፡

በቀጣይም መሠረታዊ የሥራ ሂደት ለወጥ ጥናት እንዲሳካ ጥረት በመደረግ ላይ ሲሆን በየደረጃው የሚታዩትን የማስፈጸም አቅም ችግሮች ደረጃ በደረጃ መፍታት እንዲያስችል ለክልል ሴክተር መ/ቤቶች፣ለዞኖችና ልዩ ወረዳዎች ተገቢው ክትትልና ድጋፍ ተደርጓል፡፡ በመሆኑም በሲቪል ሰርቪስ ማሻሻያ ፕሮግራም፣ በወረዳ አቅም ግንባታ ፕሮግራም፣ በፍትህ ስርዓት ማሻሻያ ፕሮግራምና በምንድስና አቅም ግንባታ ፕሮግራምና በኢንፎርሜሽን ኮሙንኬሽን ቴክኖሎጂ የተከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

## 2. የሲቪል ሰርቪስ ማሻሻያ ፕሮግራም

መሰረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥን /BPR/ በሁሉም የመንግስት ተቋማት በተጠናከረ በተሟላ ሁኔታ እንዲተገበር ድጋፍና ክትትል ለማድረግ በተያዘው እቅድ መሰረት፡- የክልላችንን የማስፈጸም አቅም ችግር ከመሰረቱ ለመፍታት እና የአገልግሎት አሰጣጥን በማቀላጠፍ መልካም አስተዳደር የማስፈን ጉዳይና ልማትን ቀጣይነት ባለው መልኩ ማረጋገጥ እንዲቻል በክልላችን መሰረታዊ የስራ ሂደት ለውጥ ጥናትን በሁለት ዙር በመክፈል ሴክቶሪያል በሆነ መልኩ እንደየሥራ ሂደቱ ሁኔታ ከክልል እስከ ቀበሌ ድረስ ድግግሞሽንና የሥራ ግጭትን በሚያስወግድ መልኩ በክልሉ ስትሪንግ ኮሚቴ እየተመራ እና በክልላዊ ቴክኒካል አማካሪ ቲም እየተደገፈ በሙከራ ትግበራ ተፈትሾ በሁሉም መንግስት መ/ቤቶች ለውጡ □□ተተገበረ □□ኛል። ቀሪ የሥራ ሂደቶች ሙከራ ትግበራ በመግባት  በአጭር ጊዜ ውስጥ ወደ ሙሉ ትግበራ እንደሚገቡ ይጠበቃል። በመሆኑም በሁሉም የመንግስት ተቋማት የመሰረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥ ያልተቋረጠ ምክርና የቴክኒካል ድጋፍ በመሥጠት በክልሉ የመሰረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥ ትግበራ በተሏላና ውጤታማ በሆነ መልኩ ተግባራዊ እንዲሆን ክትትልና ድጋፍ እየተደረገ ይገኛል።

በዚህም መሰረት ለሙከራ እና ለሙሉ ትግበራ የየራሳቸው የክትትልና ድጋፍ ቼክ ሊስት በማዘጋጀት ለመጀመሪያ ዙር ሙከራ ትግበራ ሁለት ዙር እና ለሙሉ ትግበራ ሁለት ዙር ክትትልና ድጋፍ በማድረግ ለሚመለከተው አካል ሁሉ ሪፖርት ተደርጓል። በየደረጃ ላሉ አመራሮችና ፈጻሚዎችም ግብረ መልስ ተሰጥቷል። በሁለተኛ ዙር መሰረታዊ የሥራ ሂደት ጥናት አጠናቆና ሙከራ ትግበራ በትክክል አካሂዶ ስለማጠናቀቃቸው እና ለሙሉ ትግበራ ዝግጁ ስለመሆናቸው ክትትልና ድጋፍ ተድርጎ አስፈላጊውን ግብዓት በመስጠት ወደ ሙሉ ትግበራ ለማስገባት በታቀደው መሰረት የሥራ ሂደቶች ለፈጻሚዎች ስልጠና በመስጠት ወደ ሙሉ ትግበራ እንዲገቡ ተደርጓል።

ሆኖም ገቢዎች ባለስልጣን፣ የመንግስት ኢንፎርሜሽን ኮዩሚንኬሽን ጉዳዮች ቢሮ፣ ክልል ም/ቤት እና ርዕሰ መስተዳደር ጽ/ቤት ውስጥ ያሉ የሥራ ሂደቶች የሙከራ ትግበራውን አጠናቀው የሰው ሃይል ድልድል በማከናወን ለፈጻሚዎች ስልጠና

ለመስጠት የበጀት እጥረት በማጋጠሙ ዘግይቶ በሁለተኛ ሩብ አመት ችግሩ በመፈታቱ ስልጠና  በመስጠት ትግበራ ላይ ይገኛሉ፡፡ በሌላ በኩል በሁለተኛ ዙር ጥናት አካሂደው ነገር ግን በቂ ባልሆነ ምክንያት የሙከራ ትግበራ ያላካሄዱ/ ያላጠናቀቁ ተቋማት ኦሞ ማይክሮ ፋይናንስ፣ መንገዶች ባለስልጣን፣ ወንዶ ንግድ ኩባንያ፣ ውሃ ስራዎች ድርጅት እና ብዙሃን መገናኛ ናቸው፡፡ ከነዘህ ውስጥ በሁለተኛ ሩብ አመት የመንገዶች ባለስልጣንና ወንዶ ንግድና ኢንቨስትመንት ድርጅት ወደ ሙከራ ትግበራ ገብተዋል፡፡

የሙሉ ትግበራ አፈፃፀም መመሪያና መከታተያ ቼክ ሊስት ተዘጋጅቶ ለየሴክተሮች እንዲተላለፍ ተደርጓል፡፡ በእያንዳንዱ ሴክተር ለውጡን ተቋማዊ መሠረት ለማስያዝና ሥራ ሂ□ቱ □ስከሚደርስበት የአስተዳደር እርከን ድረስ የተጠናከረ ክትትልና ድጋፍ በማከናወን ለአመራሩ ቴክኒካል ድጋፍ የሚሰጥ ተጠሪነቱ ለየሴ□ተሩ ስቲሪንግ ኮሚቴ የሆነ የክትትልና ድጋፍ ሃይል አደራጅቶ  እንዲጠቀሙ ተደርጓል፡፡ በሁለቱ ዙር ከሥራ ሂደት መለየት አንስቶ እስከ ሙሉ ትግበራ ድረስ በየመካከሉ የስልጠና፣ የክትትልና የድጋፍ ሥራ በስፋት በመስራት ለተለያዩ የሚነሱ ጥያቄዎች ለምሳሌ ሥራ ሂደቱ ታጨቀ ይከፈል፣ መለየት ሲገባ የቀረ፣ መዋሃድ ሲገባ የተነጣጠለ… ወዘተ ሲቀርቡ በርካታ ውይይቶችን በማድረግ የመፍትሄ ሃሳብ ቀርቦ ተገቢው ውሳኔ እየተሰጠ የሚያጋጥሙ ችግሮች በየደረጃ እንዲፈቱ ተደርጓል፡፡

በክልሉ በአንደኛና ሁለተኛ ዙር የመሠረታዊ ስራ ሂደት ለውጥ ጥናት የተደረገባቸው የስራ ሂደቶችን አንድን ተልዕኮ ለማሳካት የሚያስችሉ ግልጽና በቀላሉ ሊታይ የሚችል የጋራ ውጤት ያላቸው መሆኑ፣ እርስ በርስ የጠበቀ ቁርኝት፣ ተመጋጋቢና ተያያዥ (interface) ያላቸው መሆኑ፣ ለተገልጋይ አገልግሎት ለመስጠት ያለው አመችነት፣ ከክልል ተነስተው ዞንና ወረዳን አቋርጠው እስከ ቀበሌዎች ድረስ የሚዘልቁ የሥራ ሂደቶችን በአግባቡ አቀናጅቶና አስተሳስሮ ከመተግበር አኳያ ለመቋቋም የሚያስችል፣ በህገ-መንግስት የተመለከተውን  የሥልጣን ክፍፍል መሠረት በማድረግ፣ ሥራን በተሻለ ሁኔታና ቦታ መፈጸም የሚያስችል መሆኑ፣ በባህሪው ሊጣመር የማይችልና የጋራ ውጤት የማይኖረው አንድ ሥራ ሂደት ራሱን ችሎ ተቋም ሆኖ እንዲደራጁ ፕሮፖዛል በማዘጋጀት በክልሉ መሰረታዊ የሥራ ሂደት ስቲሪንግ ኮሚቴ እንዲገመገም በማድረግና የማዳበሪያ ሃሳቦች ታክለውበት በክልሉ መስተዳደር ም/ቤት ቀርቦ አቋም ተይዞበት

በክልል ምክር ቤት የክልሉ አስፈጻሚ ተቋማት አደረጃጀት አዋጅ ሆኖ ፀድቆ ተግበራዊ እየተደረገ ይገኛል፡፡

በሌላ በኩል በሥራ ሂደት ቀረጻ ወቅት የሥራ ሂደት ሆነው መቆም ያልቻሉና በአደረጃጀት ወቅት ሳይታዩ የታለፉ ነገር ግን የተቋማትን ተልእኮ ቀልጣፋና ውጤታማ በሆነ ሁኔታ በማሳካት ረገድ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያላቸውን አገልግሎቶች በመለየት ከባህሪያቸው አንፃር ማደራጀት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ በእስካሁኑ የለውጥ ሥራ ሂደት ከታዩ ተሞክሮዎች በመነሳት እነዚህን አገልግሎቶች ማለትም፤ የትራንስፖርት ስምሪት፣ ፅዳት፣ ጥበቃ፣ የመላላክ አገልግሎት፣ የአትክልተኛ እና የቤተ መጻህፍት አገልግሎት በጋራ አገልግሎቶች ሥር እንዲደራጁ በማድረግ እያንዳንዱ ሴክተር ከራሱ ተጨባጭ ሁኔታ በማደራጀት ወደ ትግበራ እንዲገቡ መነሻ ሀሳብ ለክልሉ መሰረታዊ የሥራ ሂደት ስቲሪንግ ኮሚቴ ቀርቦ ፀድቋል፡፡ በዚህ መሰረት እያንዳንዱ ሴክተር መ/ቤት በተቀመጠው ስታንዳርድ መሰረት ከመ/ቤታቸው ተጨባጭ ሁኔታ ጋር በማጣጣም እንዲያዘጋጁ እየተደረገ ይገኛል፡፡

### *ለውጡን በመተግበር የተ□ኙ ዋና ዋና ውጤቶች*

1. ለተገልጋይ የሚሰጡ አገልግሎቶች ውጣ ውረድ ሳይበዛ በአንድ ቦታ አልቆ እንዲሰጥ መደረጉ፣
2. ፈፃሚዎች ሃላፊን ሳይጠብቁ በተጠያቂነት መንፈስና በራስ ተነሳሽነት ሃላፊነት ወስደው ውሳኔ መስጠት መጀመራቸው፣
3. የሥራ ጊዜን በአግባቡ ሥራ ላይ በማዋል ረገድ መሻሻል መ□ነቱ፣
4. በቲም ስፒሪት ተተካክቶ የመሥራት ልምድ እየዳበረ መሆኑ፣
5. ተገልጋይን ፈጥኖ የማስተናገድና መረጃን የመስጠት አፈፃፀም መሻሻል □□□ መሆኑ፣
6. የሥራ ሂደትን መሰረት ያደረጉ ተቋማት መመስረታቸው …ወዘተ ናቸው፡፡

በአጠቃላይ በክልሉ ለውጡ ያለበት አፈጻጸም፣ ክትትል፣ ድጋፍና መረጃ አያያዝ ደረጃ ሲታይ በመጀመሪያ ዙር ወደ ሙሉ ትግበራ ከገቡ ሴክተሮች ንግድና ኢንዲስትሪ እንደሴክተር፣ ወንጀል መካለከልና የህብረተሰብ ሰላም ማስጠበቅ እና ማረምና ማነጽ

የሥራ ሂደቶች እንደ ሥራ ሂደት በአንጻራዊ የመጀመሪያ ደረጃ፤ አቅም ግንባታና ትምህርት ሴክተሮች በሁለተኛ ደረጃ አፈጻጸም እንደሚገኙ በተለያየ ጊዜ በተደረገ ክትትልና ድጋፍ መረጃ ለማየት ተችሏል፡፡ በሌላ በኩል ከተማ ልማት ሴክተር በተለይም ማዘጋጃ ቤቶች እና ግብርናና ገጠር ልማት ሴክተር እንደሴክተር ለውጡን መተግበር በጥናቱ መሰረት አለመጀመራቸው ብቻ ሳይሆን ያሉበት ደረጃ ተገምግሞ ግብረ መልስ ተሰጥቶአቸው የማሻሻያ እርምጃ የመውሰድ ሁኔታ አለመተየቱ አሳሳቢ ነው፡፡ ይህ ሁኔታ በአስቸኳይ ታርሞ በነዚህ ሴክተሮች ለውጡ በጥናቱ መሰረት ወደ ትግበራ ካልገባ አጠቃላይ ለውጡ ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ከማሳደር ባሻገር □□ልሉ መንግሥት እየሠራ ላለው ፈጣን ልማት የማረፉ□□፣ ዲሞክራሲንና መልካም አስተዳደርን የማስፈን ጥረትን ሊያደነቅፍ ይችላል፡፡ በሌላ በኩል ፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ሴክተር የተዘበራራቀ አፈጻጸም ላይ ይገኛል፡፡ በተወሰኑ የዞንና የወረዳ አካባቢዎች ከቀድሞ የተሻለ አፈጻጸም የታየ ቢሆንም አብዛኛዎቹ ዞኖችና ወረዳዎች እንዲሁም ክልል መ/ቤቶች ለውጡን ያልተከተለ እና በጥናት ሰነዱ የተመለከተው ስታንዳርድ መሰረት እየተፈጸመ አይደለም፡፡ ለአብነት በፐርፎርማ ግዥ መፈጸም፣ የጥራት ደረጃውን ያልጠበቀ ዕቃ መግዛት፣ በጥናት ሰነዱ በተመለከተው የጊዜ ስታንዳርድ ደረጃ መሠረት ግዥ ተፈጽሞ ካለማቅረብ ጋር ተያይዞ የተገልጋይ ቅሬታ በስፋት መቀጠሉ የመሰሳሉ ችግሮች ይታያል፡፡ አቤቱታ መመርመር፣ መክሰስ፣ መስማትና መወሰን የሥራ ሂደት ከጥናት እስከ ሙከራ ትግበራ በጥሩ ሁኔታ የተመራ ቢሆንም ወደ ሙሉ ትግበራ ሲገባ ጀምሮ የተወሰነ መዝረክረክና የአመራር ተቀናጅቶና ተደራጅቶ ያለመምራት ችግሮች ታይቶበታል፡፡

የለውጡ አፈጻጸም ደረጃ በሁለተኛ ዙር ትግበራ ከገቡ ሴክተሮች አንጻር ሲታይ በጥናት ጊዜ በአብዛኞቹ ሴክተሮች አመራር ጥሩ የሚባል ድጋፍና ክትትል የነበረ ቢሆንም ጥናቱን በሙከራ ትግበራ ጭምር የተሻለ ድጋፍና ክትትል ያደረጉ ሴክተሮች የገቢዎች ባለስልጣን፣ ጤና፣ የመንግስት ኮሚዩንኬሽን ጉዳዮች እና አርብቶ አደር ጉዳዮች ቢሮ ከሌሎቹ በአንጻራዊ ሁኔታ አመራሩ የተሻለ ክትትልና ድጋፍ ሲያደርግ የቆየ ሲሆን ሌሎቹ ሴክተር መ/ቤቶች አመራር ቀጣዩን ደረጃ ይይዛል፡፡ በሌላ በኩል ከላይ እንደተገለፀው ጥናታቸውን እንደምንም ቢያጠናቅቁም እስከአሁን በቂ ባልሆነ ምክንያት የሙከራ ትግበራ ያላካሄዱ/ ያላጠናቀቁ ተቋማት (ኦሞ ማይክሮ ፋይናንስ፣ መንገዶች

ባለስልጣን፣ ወንዶ ንግድ ኩባንያ፣ ውሃ ስራዎች ድርጅት እና ብዙሃን መገናኛ) በሦስተኛ ደረጃ የሚፈረጁ ናቸው፡፡

በአጠቃላይ ከላይ በተወሰነ መልኩም ቢሆን የቀረቡ ችግሮችን በጥልቀት አይቶ የማስተካከያ እርምጃ ካልተወሰደ በስተቀር ችግሩ መቀጠሉ የማይቀር እንደሆነ ለመረዳት ይቻላል፡፡

የመሰረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥ ዳይመንዱን የተሟላ ለማድረግ ከፌደራል ተጠንተው በሚወርዱ የጥናት ውጤቶች ከክልሉ ተጨባጭ ሁኔታ ጋር በማስማማት የተዘጋጀና ሥራ ላይ ለማዋል በተቀመጠው ግብ፡- ከመሠረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥ (BPR) ትግበራ የተነሳ በተቋማት አደረጃጀት፣ አሠራርና በሰው ኃይል አስተዳደር ላይ አያሌ ለውጦች ተከስተዋል፡፡ በአደረጃጀትና በአሠራር ረገድ የታዩ ለውጦች በሂደት በተለያዩ የህግ ማዕቀፎች ምላሽ እያገኙ በመሄዳቸው በለውጡ ላይ በጐ ተፅዕኖ እያሳደሩ መሆኑን መገንዘብ ተችሏል፡፡ ነገር ግን በሰው ኃይል ምደባና አስተዳደር በኩል የታዩ ለውጦችና ክፍተቶች ወቅታዊ የሆኑ ምላሽ ያላገኙ በመሆናቸው በሰው ሃይል አስተዳደር ላይ ችግሮች እየፈጠሩና በለውጡ ሂደት ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ እያሣደሩ ቢሆንም የመሠረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥ ትግበራ ከተጀመረ በኋላ ቅጥርና ዝውውር ታግዶ የነበረውበመነሳቱ የሥራ ሂደቶች በዲኘሎማና በዲግሪ መነሻ ደመወዝ ቅጥር እየተከናወነ ይገኛል፡፡

ይሁን እንጂ የደረጃ ዕድገት መታገድና አዲስ ቅጥር መፈቀዱ በሰው ኃይል አስተዳደር ላይ ክፍተት ፈጥሯል፡፡ ይኸውም የደረጃ ዕድገት መታገዱ በአነስተኛ መደብ ላይ የነበሩ ሠራተኞች የትምህርት ዝግጅታቸውን አሻሽለው ምደባ ያገኙ በያዙት ደመወዝ ለዲኘሎማና ለዲግሪ ከተፈቀደው መነሻ በታች በቀድሞ ደመወዛቻው እየሰሩ ሲሆኑ በሌላ አንፃር በዜሮ አገልግሎት በአዲስ ቅጥር የተቀጠሩ የመነሻ ደመወዝ እያገኙ እንዲሰሩ መደረጉ በሰራተኛው ተነሳሽነት ላይ ተጽኖ አሳድሯል፡፡

ስለዚህ የሀገር አቀፍ የአቅም ግንባታ ስትሪንግ ኮሚቴ በ18/01/2002ዓ.ም ባደረገው የቪዲዮ ኮንፍራንስ ስብሰባ ላይ ይህን ሁኔታ አስመልክቶ የደረሰበት ስምምነት

እንደሚገልፀው አጠቃላይ የሆነው  የደረጃ ዕድገት ሀገር አቀፍ የሆነው የሥራ ምደባና ደረጃ አወሳሰን ሥርዓት ሥራ ላይ ሲውል ምላሽ ሊያገኝ የሚችል መሆኑን አመልክቶ በዝቅተኛ የሥራ መደብ ላይ የነበሩ ሠራተኞች የትምህርት ዝግጅታቸውን በዲኘሎማና በመጀመሪያ ዲግሪ ደረጃ አሻሽለው ምደባ ያገኙና ከዜሮ ዓመት አገልግሎት የዲኘሎማና የመጀመሪያ ዲግሪ የመነሻ ደመወዝ በታች ይዘው በአሁኑ ሰዓት እየሠሩ ላሉ ደመወዛቸው እንዲስተካከል አቅጣጫ ባማስቀመጠው መሰረት በክልላችን ይኸው ችግር ጐልቶ የሚታይ በመሆኑ ማስተካከል ተገቢ በመሆኑ ዲኘሎማ፣ የመጀመሪያ ዲግሪና ሁለተኛ ዲግሪ አቅርበው ምደባ ላገኙ እና ለዲኘሎማ፣ ለመጀመሪያ ዲግሪና ሁለተኛ ዲግሪ ከተፈቀደው መነሻ ደመወዝ በታች እየተከፈላቸው ላሉ ሠራተኞች መነሻ ደመወዝ እንዲስተካከል ለመስተዳድር ም/ቤቱ ችግሩን የሚያሳይና መፍትሄ ሀሳብ የያዘ ጥናት ተጠንቶ ቀርቧል፡፡

በሌላ በኩል በፌደራል ደረጃ የተዘጋጀውን ጥናት መነሻ በማድረግ  ከክልላችን ተጨባጭ ሁኔታ ጋር በማገናዘብ ከሥልጣን ለሚነሱ የክልሉ ከፍተኛ መንግስት ባለስልጣናት ጥቅማ ጥቅም ማስጠበቂያ ሥርዓት ፖሊሲ ረቂቅ ሰነድ ተዘጋጅቷል፡፡ እንዲሁም በክልሉ ምርጥ ተሞክሮ መቀመርና መስፋፊያ ስራ ወጥነት የጎደለው በመሆኑና የግንዛቤ ክፍተትም በመኖሩ ይህን ችግር የሚፈታ የክልሉ ምርጥ ተሞክሮ ማቀመርያና መስፋፊያ ስትራቴጂ ሰነድ ረቂቅ ተዘጋጅቷል፡፡

የሙሉ ትግበራውን አፈፃጸም የሚደግፉ የትግበራ ስትራቴጂ □ና የሰው ሃይል ድልድል ደንብ ሠነዶች ተከልሰው የግንዛቤ ማዳበሪያ ገለፃና ውይይት ተደርጎባቸው ሥራ ላይ □ሏል፡፡ የሥራ ሂደቶቹ ሲጠኑ አላሰራ ያሉ ህጎችን በመለየት ለህጎቹ መውጣት ምክንያት የሆኑ ታሳቢዎች  የተሰበሩ በመሆኑና በአዳዲስ ታሳቢዎች የተኩ የሰው ሀብት ሥራ አመራር መመሪያዎችና መስፈርቶች ተዘጋጅቷል፡፡ ከዚሁ አንጻርም □ቀ□ሞ□ የምልመላና መረጣ መመሪያ ተሽሮ የሰው ሀብት የማሟላት አፈፃፀም መመሪያን በአዲስ ሁኔ□ በማዘጋጀትና ተገልጋዮችንና ባለድርሻ አካላትን በማወያየት ተገቢው ግብዓት ተካትቶበት በሴ□ተር ደረጃ □□ቆ ሥራ ላይ ውሏል፡፡

በሰው ሃብተ ሥራ አመራር ዋና የሥራ ሂደት በትግበራ ወቅት ያጋጠሙ ችግሮችን ለመለየት በተደረገ ድጋፍና ክትተል በሴክተሮች የሰው ሃብተ ሥራ አመራር ዴጋፊ የሥራ ሂደት ሲደራጅ አንድ ሰው ብቻ መሆኑ በወሳኔ አሰጣጥ ሊኖር የሚችል ክፍተትን በመለየት  አንድ ሰው ተጨማሪ እንዲሆን ለቢሮው ለውሳኔ ሃሳብ ቀርቧል፣ ተደራሽ ግቦች በትግበራ ሲፈተሹ ክፍተቶች በማጋጠሙ የጥናቱን ዶክመንት ለማሻሻል አስፈላጊው መረጃ ተደረጅቶ  ለውሳኔ ቀርቧል። የመንግስት ሠራተኞች ጥቅማጥቅምና የተፈላጊ ችሎታ መመሪያ ለማዘጋጀት መረጃ የማሰባሰብና የመተንተን ሥራ ተሰርቷል፣ በክልሉ የተለያዩ የሥራ ሂደቶች የሰው ሃይል ማሟለት ጥያቄን በመቀበል ቅጥር ተፈጽሟል፣ የአገልግሎት ማቋረጥ መመሪያ ለማዘጋጀት መረጃ የማሰባሰብና የመተንተን ሥራ ተሰርቶ የመጀመሪያ ረቂቅ ተዘጋጅቷል፣ በሩብ አመቱ 198 ጉዳዮች የምክር አገልግሎት ለመስጠት ታቅዶ 292 ምክርና ማብራሪያ ተሰጥቷል።

ቀደም ሲል ይሰጥ የነበረው የጠቅላላ አገልግሎትና የጥገ ሥራዎች በለቤት ለመሥጠት የመፍትሄ አቅጣጫ ጠቋሚ ንድፈሃሳብ ቀርቧል፣ የሠራተኞች ሣዓት መቆጣጠሪያ ፎርማት በማዘጋጀትና በሴክተሩ ስትሪን ኮሚቴ በማጸደቅ ሥራ ላይ እንዲውል ተደርጓል። በቀጣይም ችግሩን በዘላቂነት ለመፍታት የጋራ አገልግሎቶች በሚል ተጠንቶ ለሌሎች ሰባት ሰክተሮች ባቀረቡት የሰው ሃይል ጥያቄ መሰረት ተፈቅዶ መመሪያው እንዲተላለፍ ተደርጓል፣ የቀበሌ ሥራ አሥኪያጆች መመሪያ ከመንግሥት ሠራተኞች አዋጅ 47/94 አንፃር ማሻሻያ ሐሳብ ቀርቧል፣ የሰራተኞች የዝውውር ዕገዳ እንዲነሳ የውሳኔ ሃሳብ ፕሮፖዛል ቀርቦ ዕገዳው እንዲነሳ ተደርጓል፣የኢንተርፕራይዞች ልማትና የራሥ ሥራ ፈጠራ ድጋፍ አሰጣጥ የሥራ ሂደት ለኤጀንቶችና ፋሲሊቴተሮች ታግዶ የነበረው እንዲለቀቅ ባቀረቡት ጥያቄ ውይይት ተደረጎበት በመታመኑ ጥቅማጥቅሙ እንዲፈቀድላቸው ተደርጓል፣የጋራ አገልግሎቶች አስተባባሪ ተጠሪነቱ በየደረጃው ላለው የሰው ሃብት ሥራ አመራር እንዲሆን የሚል የውሳኔ ሃሳብ ቀርቧል፣ለደሮ እርባታ ማዕከሎች የቀረበውን የጠቅማጥቅም ጥያቄ አስፈላጊነቱ ታምኖበት ጥቅማጥቅሙ ተፈቅዷል፣የሰራተኛ ቅጥር በሚፈቀድበት ወቅት የአገልግሎት ማስረጃ ኣያያዝን አስመልክቶ ለ29 መ/ቤቶች ሰርኩላር ተላልፏል ሌሎች ማብራሪያ የሚሹ ከክልል ሴክተር መ/ቤቶች ለቀረቡ ጥያቄዎች ተገቢው ማብራሪያና ምላሽ ተሰጥቷል።

አዘገጃጀት፣የለውጥ አመራር፣የሂሳብ አያያዝ የስልጠና ሞጅሎች የማሻሻል ሥራተሠርቷል፡፡

በትራንስፎርሜሽን ሊደርሺፕ 19 ባለሙያዎች የአሰልጣኞች ስልጠና ወስደዋል፣ ከኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ኮሌጅ በተገኙት የትምህርት እድል 47 እጭዎች የእድሉ ተጠቃሚ ሆነዋል፣ የዉጭ ሀገር የትምህርትና ስልጠና ለሁለት ባለሙያዎች የትምህርት እድል የማመቻቸት ስራ ተከናዉኗል፡፡

በክልሉ የመሰረታዊ አሰራር ሂደት ለዉጥ ተግባረዊ ሲደረግ ምደባ ያላገኙ ሰራተኞች የትምህርት እድል አማራጭ ተጠቃሚ እንዲሆኑ በወጣዉ መሰረት የ 794 ሰራተኞች መረጃ ተደራጅቷል፡፡ አመራር ተቋም አመራርና ፈፃሚዎች የተወጣጣ አንድ ቡድን በፌደራል፤ በአማራ ክልል እንዲሁም በትግራይ ክልል ባደረገዉ የልምድ ልዉዉጥ ጠቃሚ ተሞክሮዎች ተገኝቷል፡፡

### 3. ያልተማከለ የወረዳ አስተዳደር ፕሮግራምና የመልካም አስተዳደር ፓኬጅ

በክልሉ በሁሉም ወረዳና ቀበሌ የመልካም አስተዳደር ፓኬጅ ተግባራዊ ለማድረግ የተያዘ ግብ፡- በክልሉ በሁሉም ወረዳና ቀበሌ የመልካም አስተዳደር ፓኬጅ ተግባራዊ ለማድረግ የእንስፔክሽን አደረጃጀትና አሰራር ስርዓትን ለመዘርጋት በታቀደው መሰረት የኢንስፔክሽን እና የሱፐርቪዥን አፈጻጸም ማኑዋል ተዘጋጅቶ ለሁሉም ዞን፣ ወረዳና ቀበሌ ሰነዱ ተበዝቶ ተሰረጭቷል፡፡ የተዘጋጀውን ሰነድ ለ13 ዞንና ለ8 ልዩ ወረዳ የአቅም ግንባታ ኃላፊዎች በተዘጋጀው የኢንስፔክሽን ማኑዋልና የሥራ አስኪያጅ መመሪያ ላይ የአስልጣኞች ስልጠና በመስጠት 3419 የገጠር ቀበሌ ሥራ አስኪያጆችን እንዲያሰለጥኑ ተደርጓል፡፡

በሁሉም ቀበሌያት የቀበሌ ሥራ አስኪያጅ በተጠናከረ ተቋማዊ መዋቅር እንዲሰራ በመደረጉ ሕብረተሰቡ የሚፈልገውን አገልግሎት ፈጣን ምላሽ ማግኘት ተችሏል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የቀበሌ ሥራ አስኪያጆች ዘወትር ለአገልግሎት የሚመጣውን አርሶ አደር ተገቢውን አገልግሎት እንዲያገኙ ከማድረግ ባሻገር በሚሰጥ አገልግሎት ለሚፈጠር ቅሬታ አስተያየት መስጫ ቅጻቅጾችና መዛግብት ተዘጋጅቶ አስተያየት በማሰባሰብ አገልግሎትን ለማሻሻል ውይይት ማድረግ ተችሏል፡፡ በአንዳንድ የገጠር ቀበሌዎች

የቀበሌ ሥራ አስኪያጅ የመንግሥት መዋቅር ተቀጥረው የሚሰሩ የግብርናና የጤና ሠራተኞች የሥራ ሣዓት መቆጣጠር ተጀምሯል፡፡ ሥራ በለቀቁና ኃላፊነታቸውን በማይወጡ የቀበሌ ሥራ አሥኪያጆች የማሟያ ቅጥር በመፈጸም በቀበሌው የሚሰጠው አገልግሎት እንዳይቋረጥ ተደርጓል፡፡ አዲስ ቅጥር በተፈጸመባቸው ለሁሉም ቀበሌያት አዲስ ለተቀጠሩ ሥራ አስኪያጆች በወረዳ ማዕከል ሥልጠና ተሰጥቷል፡፡ በአንዳንደ ዞኖች የቀበሌ ሥራ አስኪያጆች እንቅስቃሴ በመገምገም ችግር ያለባቸውን በመለየት የማስተካከያ እርምጃ ተወስዷል፡፡ ስለሆነም የተያዘው ዕቅድ በተያዘለት የጊዜ ገደብ መሰረት ተከናውኗል፡፡

የመልካም አስተዳደር ፓኬጅን በሁሉም የአርብቶ አደር ወረዳና ቀበሌ ከአካባቢው ተጨባጭ ሁኔታ ተስማሚ ተድርጎ ለመተግበር ከተዘጋጀ በኂላ በክልሉ መስተዳደር ም/ቤት ፀድቆ ለተሟላ ትግበራ የአፈጻጸም መርሐ-ግብር በማዘጋጀት ተግባራዊ ማድረግ እንዲቻል በቅድሚያ ለአርብቶ አደር ዞንና ወረዳ አመራር ስልጠና ለመስጠት አስፈላጊው የሥልጠና ቅድመ ዝግጅት ስለተጠናቀቀ ወደ 3ኛ ሩብ አመት መጀመሪያ ላይ እንዲተገበር መርሃግብር ተዘጋጅቷል፡፡

## 4. የፍትህ ሥርዓት ማሻሻያ ፕሮግራም

በክልሉ የፍትህ ሥርዓት ማሻሻያ ፕሮግራምን ስኬታማነትና ውጤታማ ለማድረግ የፍትህ አካላትን በስልጠና ለማብቃትና ተkማቱን በሰው ሃይልና በማቴሪያል ለመደገፍ በታቀደው መሰረት ከአርብቶ አደር አካባቢ ተመልምሎ በመደበኛ ፕሮግራም የህግ ትምህርት ለሚያጠኑ 100 ዲፕሎማ ተማሪዎች ከዛየን ቴክኖሎጂና ቢዝነስ ኮሌጅ ጋር ውል ስምምነት በመፈጸም ከሀምሌ ወር ጀምሮ ትምህርታቸውን እንድከታታሉ ተደርጓል፡፡

በሌላ በኩል የፍትህ ተቋማትን ቀልጣፋ፣ ውጤታማ እና ተደራሽ ለማድረግ በመሠረታዊ የስራ ሂደት ለውጥ ጥናት የአቤቱታ መመርመርና ዉሳኔ መስጠት የሥራ ሂደት ከሙከራ ወደ ሙሉ ትግበራ በማሸጋገር የፍትህ አሰጣጡ ተደራሽ ወጪ ቆጣቢና ጥራት ያለው እንዲሆን ፍ/ቤቶች ተዘዋዋሪ ችሎት እያስቻሉ ይገኛሉ፡፡

በግማሽ ዓመቱ በአንደኛ ዙር በፍትህ ማሰልጠኛና ምርምር ተቋም አቃቤያንና ዳኞች የሰለጠኑ ሰልጣኞችን በማስመረቅ ወደ ሥራ እንዲሰማሩ ተደርጓል፡፡ በ2ኛ ዙር በማሰልጠን ላይ ያሉ የህግ ባለሙያዎች በአቃቤ ህግ ደረጃ ማከናወን የሚገባቸውን

የሶስት ወራት የሥራ ላይ ልምምድ አጠናቅቀው ቀጣይ የስድስት ወራት ደግሞ በዳኝነት የሥራ ላይ ልምምድ ማድረግ የሚችሉበት ሁኔታ ተመቻችቶ ወደ ሥራ እንዲሰማሩ ተደርጓል፡፡ ለዚህም ተቋሙ የመስክ ግምገማ በማድረግ ግብረ መልስ ሠልጣኞችች እንዲያገኙ አድርጓል፡፡ በሌላ በኩል ከህዳር 1/2002 ጀምሮ በዲግሪ 110 እና በዲፕሎማ 50 በድምሩ 160 ሠልጣኞች የሦስተኛ ዙር የህግ ባለሙያዎች ስልጠና ገብተዋል፡፡

በክልሉ የህግ ጥናትና ምርምር በተጠናከረ መንገድ ተግባራዊ ለማድረግ እንዲቻል የክልሉ የፍትህ አካላት የሥልጣን ማዕከል እና ከሐዋሳ ዩኒቨርስቲ የህግ ፋካሊቲ ጋር በቅንጅት መስራት በሚቻልበት አግባብ ላይ ስምምነት ተፈራርሟል፡፡ በተቋሙና በክልሉ ለሚገኙ የህግ ባለሙያዎች አጫጭር ስልጠናዎችን ለመስጠት በታቀደዉ መሰረት በዩኒሴፍ ድጋፍ 15 ዳኞች እና ለ15 አቃቤ ህግ ባለሙያዎች በድምሩ 30 ሰልጣኞች በህጻናት ፍትህ ላይ ለ10 ቀናት ሥልጠና እንዲሰጥ ተደርጓል፡፡

በሁሉም የክልሉ አስተዳደር እርከን የተዘዋዋሪ ችሎት ቁጥር እንዲጨምር በማድረግ ህብረተሰቡ ከምርት ስራው ሣይለይ ፍትህ እንዲያገኝ አስፈላጊው ድጋፍ ተደርጓል፡፡ በሃድያ ዞን 220 ለሚሆኑ የምርመራ፣ ክስ አመሰራረትና ውሣኔ አሰጣጥ የሥራ ሂደት ባለሙያዎች ስልጠና ተሰጥቶ ከፍትህ ተቋማት ጋር በጋራ የድጋፍና ክትትል ሥራ ተሰርቷል፣ ቤንች ማጂና ወላይታ ዞን የእጅ ከፍንጅ የተያዙ ወንጀለኞች የዕለት ፍርድ እንዲሰጥ በተደረገው ስምምነት መሰረት ወዲያውኑ ውሣኔ መስጠት እንዲቻል ድጋፍና ክትትል ሥራ ተሰርቷል፡፡ የፍትህ አገልግሎት አሠጣጥ ቀልጣፋና ውጤታማ ለማድረግ የጋራ ጥምር ሥራ አመራር ኮሚቴ እንዲሰራ ተገቢው ድጋፍና ክትትል ተደርጓል፡፡

በሁሉም ቀበሌያት የኮሚኒቲ ፖሊሲንግ ሥርዓት እንዲዘረጋ ድጋፍና ክትትል ሥራ ለመሥራት በተያዘ ዕቅድ መሰረት፡- ከፍትህ ተቋማትና ከፖሊስ ጋር በመቀናጀት የኮሚኒቲ ፖሊሲንግ ባልተቋቋመባቸው በሁሉም ከተማና የገጠር ቀበሊያት እንዲቋቋም ተደርጓል፡፡ 5094 ለሚሆኑ የህብረተሰብ ክፍል በኮሙኒቲ ፖሊሲንግ ስልጠና አንዲሰጥ ተገቢው ድጋፍ በመደረጉ ህብረተሰቡ የራሱን ሰላም ማስከበር ሥራ ላይ ተሳታፊ እእንዲሆን አስችሏል:: በየዞኑ የፍትህ ሴክተር ወንጀል መከላከልና የህብረተሰብ ሠላም ማስጠበቅ ዋና የስራ ሂደትና የኮሙኒቲ ፖሊሲንግ በሁሉም ቀበሌ እንዲደራጅ በግብ

ስምምነት ተፈራርመዋል፡፡ ህብረተሰብ ያሳተፈ የወንጀል መከላከል ሥራ በመሰራቱ በተወሰኑ ፖሊስ ጣቢያዎች የታሣሪ ቁጥርና ወንጃል ቀንሷል፡፡

በክልሉ በሥራ ላይ ላሉት ፖሊሶችን የአቅም ለመገንባት ታስቦ ለ885 ለመደበኛ ፖሊስና የማረሚያ ፖሊስ አባላት  የአጭር ጊዜ ሥልጠና ተሰጥቷል፡፡ በሌላ በኩል የልዩ ኃይል ሥልጠና በክልሉ ፖሊስ ኮሌጅ ለ644 የፖሊስ አባላት የ3 ወር ማጠናከሪያ ሥልጠና በመከታተል ላይ ናቸው፡፡ በኮሚኒቲ ፖሊሲንግ ኦፊሰርነት በተለያዩ የትምህርት ዘርፍ ዲፕሎማና ከዚህ በላይ የትምህርት ደረጃ ያላቸውን ከክልላችን 183 ከጋምቤላ፣ ከክልል 20 የፖሊስ አበላት ክፍተት ለመሙላት በፖሊሲ ኮሌጅ አጭር ጊዜ ሥልጠና እንዲወስዱ ተደርጓል፡፡ አጠቃላይ የክልሉን ነባር የፖሊስ አባላት አቅማቸውን ለማሳደግ በተለያዩ የሥልጠና መስክ 2820 ነባር የፖሊስ አባላትና የፖሊስ አመራር አካላት በተለያዩ የማሠልጠኛ ተቋማት ሥልጠና እንዲወስዱ ተደርጓል፡፡

የፍትህ ሥርዓቱን ለማጠናከር በሁሉም ዞን ማዕከል  ቼክሊስት በማዘጋጀት ድጋፋዊ ክትትል ተደርጓል፡፡ በወላይታ ዞን ሥር ላሉ ለሁሉም ወረዳዎች በሰንቴሪያ /ኮሙኒቲ ፖሊሲንግ/ ወንጀል መከላከል ዙሪያ ሥልጠና ተሰጥቷል፡፡ በጋሞ ጎፋ ዞን የኮሙኒቲ ፖሊሲንግን አሠራር ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችል በዞን ደረጃ ማስፈጸሚ ማኑዋል ተዘጋጅቶ ለሁሉም ወረዳና ቀበሌ ተሰራጭቷል፡፡ እንዲሁም በአዋሳ ከተማ አስተዳደር ከስምንቱ ክፍለ ከተማ ለተወጣጡ የሚመለከተቸው አካላት (የፖሊስ ጽ/ቤት ኃላፊዎች፣ የኮሚኒቲ - ሊሲንግ ኦፊሰሮች፣ ዋና አስተዳዳሪዎች፣ የፍትህና ፀጥታ ኃላፊዎች፣ የህዝብ ግንኙነት ኃላፊዎች፣ የፖሊስ መምሪያ ኃላፊ እና የወንጀል መከላከል የሥራ ሂደት ኃላፊዎች ጋር በጋራ በኮሙኒቲ ፖሊሲንግ ዙሪያ ውይይት በማድረግ ስራውን ለማጠናከር በስምምነት ላይ ተደርሶ ወደ ትግበራ ተገብተዋል፡፡

## 5. □ምህን□ስና አቅም □ንባ□ □ሮ□ራም

በምህንድስና አቅም ግንባታ ፕሮግራም የመንግስትና የግሉን ሴክተር ለማጠናከር የተደረገ ድጋፍና ክትትል:- ኘሮግራሙ የሪፎርም ኘሮግራም እንደመሆኑ መጠን በሌሎች ባለድርሻ አካላት የሚተገበር ኘሮግራም በመሆኑ በዚሁ መሠረት ከባለድርሻ አካላት ጋር

በመነጋገር በ2002 ዓ.ም ዕቅዳቸው ውስጥ አካተው መተግበር እንዲችሉ ለማድረግ በተደረገው ጥረት ከግብርናና ገጠር ልማት ቢሮ፣ ከንግድና ኢንዱስትሪ ቢሮ፣ ከቴ/ሙ/ት/ሥ/ተቋም ውስጥ ከሚመለከታቸው የሥራ ሂደቶች እቅድ ውስጥ እንዲካተት ተደርጓል፡፡ የምህንድስና አቅም ግንባታ ኘሮግራም ሁለተኛው የስትሪንግ ኮሚቴ ስብሰባ ያካሄድ ሲሆን ኘሮግራሙም በየባለድርሻ አካላት በበጀት የተደገፈ ሥራ እየተሰራ መሆን አለመሆኑን በተመለከተ ትኩረት ተሰጥቶበት ሊሰራ እንደሚገባውም መተማመን ላይ ተደርሷል፡፡ የምህንድስና አቅም ግንባታ ፕሮግራም በየደረጃ ላለው ለዞን፣ ለወረዳ እና ለከተማ አስተዳደር አስፈጻሚ አካላት ስለፕሮግራሙ አጠቃላይ ግንዛቤ ለመፍጠር የሚረዳ የአሰራር ማኑዋል በረቂቅ ደረጃ ተዘጋጅቷል፡፡

የጥርብ ድንጋይ ንጣፍ ሥራን በተመለከተ በክልሉ በሚገኙ 22 የሪፎርም ከተሞች ሥራውን መስራት እንዲችሉ የከተማ አስተዳደር ኃላፊዎችና ባለሙያዎች ከእያንዳንዱ ከተማ አስተዳደር ሁለት አባላት እንዲሳተፉ ሲደረግ በአጠቃላይ ሶስት ቦታ በሐዋሣ፣ ሶደና ወልቂጤ ከተሞች ስልጠናው የተሰጠ ሲሆን የሥልጠናውም ትኩረት የዕቅድ አወጣጥና ሥራውን ለመምራት የሚያስችል ስልጠና ሆኖ በውጪ ባለሙያዎች በስፋት እንዲሰጥ ተደርጓል፡፡ በክልሉ ከሚገኙ 22 የሪፎርም ከተሞች በ21 ከተሞች በ2002 ዓ.ም በጀት ዓመት ዕቅዳቸው ውስጥ እንዲካተት ተደርጓል፡፡

በዚህ ሩብ ዓመት በሐዋሳ ከተማ 2.5 ካሬ ኪሎ ሜትር ፣በዲላ ከተማ 2 ካሬ ኪሎ ሜትር ፣ ሶዶ ከተማ 9917 ከሬ ሜትር፣ አርባምንጭ 3.36 ካሬ ኪሎ ሚትር፣ አላባ ከተማ 2100 ካሬ ሜትር፣ ሆሳዕና 1200 ካሬ ሜትር መንገድ የተሰራ ሲሆን 6709 ሠራተኞች በሥራው ተሣትፈዋል፡፡

እሴት ሰንሰለት / Value chain / በተመለከተ የቆዳና ሌጦ ጥራትን በተመለከተ ከፌዴራል የምህንድስና አቅም ግንባታ የዘርፉ ባለሙያና ከግብርናና ገጠር ልማት በፌዴራል ምርምር ኢንስቲትውት የተገኙ ባለሙያዎች በዘርፉ ያለውን ችግር በመግለፅ ከፍተኛ ትኩረት የሚያስፈልገው መሆኑንና የክልሉ መንግስት ትኩረት ሰጥቶ ተገቢው በጀት እንዲመድብለት ውይይት ተደርጎበታል፡፡

በግል ተቋማት ዙሪያ የሚሰሩት የእሴት ሠንሰለት ሥራ አጠናክሮ ለመቀጠል እንዲቻል አንድ ባለሙያ በቀርከሃ ልማትና ምርት ጥራት ላይ ለመሥራት የተላከው ባለሙያ በግብርናና ገጠር ልማት ቢሮ መሥራት እንዲቻል ቢሮና የቢሮ መገልገያ ቁሳቁስ ማግኘት እንዲችል ተደርጓል፡፡

በዝንጅብል ምርት የተሰማሩ ባለሃብቶች በአካባቢው በመሬት አቅርቦት ዙሪያ ተፈጥሮ የነበረው አለመግባባት ከክልሉ ንግድ ኢንድስትሪ ቢሮ ጋር በመሆን ችግሩ የሚቃለልበት ሁኔታ እንዲመቻች ተደርጓል፡፡

በቴክኒክና ሙያ ሥልጠና ተቋም የመምህራን ብቃት ማረጋገጫ ምዘናንና ሥልጠናን በተመለከተ 196 መምህራን በደረጃ “C” በአዳማ የሥነ መምህራንነት ሥልጠና እንዲወስዱ ተደርጓል፡፡ ለ71 የቴክኒክና ሙያ ሥልጠና ተቋም መምህራን ለሦስት ሣምንታት በተለያዩ የሙያ መስኮች ሥልጠና ተሰጥቷል፡፡

በክልል ደረጃ የተቋቋመው ካውንስልና በየተቋማቱ ለተቋቋሙት ቦርድ አካላት መተዳደሪያ ደንቦች ተዘጋጅተው ተሠራጭተዋል፡፡ የካውንስልና የቦርድ አባላት በሠነዱ ላይ በቂ ግንዛቤ እንዲጨብጡ ተደርጓል፡፡ የክልሉ የልህቀት ማዕከል /COC/ አጠቃላይ ገጽታውንና አሠራሩን በተመለከተ በክልሉ በሚገኙ ኢንዱስትሪዎች በ12 ከተሞች የሚገኙ 40 የሚሆኑ መስሪያ ቤቶችና ባለድርሻ አካላትን የሸፈነ የማስተዋወቅ ብሮሸር የማደልና ግንዛቤ የማስጨበጥ ሥራ ተከናውኗል፡፡

ሥርዓተ ትምህርት ላልተዘጋጀላቸው ሙያዎች ስርዓተ ትምህርት ማዘጋጀትና TTLM ተዘጋጅቷል፡፡ የቀርከሃ ሥራ የሙያ ደረጃ ምደባ በመከናወን ላይ ይገኛል፡፡ የበርበሬና የእንሰት ውጤቶች በዘመናዊ መንገድ የማቀነባበር ሥራዎች የሙያ ደረጃ ምደባ ለማውጣት በአንድ ክላስተር ውስጥ ቅድሚያ ተሰጥቶት ሥራው በጅምር ላይ ይገኛል፡፡በሌሎች ሙያዎች  ማለትም ዳቦና እንጀራ ጋገራ፣ ደረቅ ምግብ ዝግጅት፣ ፀጉር ሥራና ውበት እንዲሁም እፅዋትና እንስሳት ተረፈ ምርት በአካባቢ ሙያነት ተለይተዋል፡፡ የቆጮ መፋቂያ በሀዋሣ ቴ/ሙ/ት/ሥ/ኮሌጅ ተሠርቶ ተጠናቅቋል፣ ሁለት የመንግስት የቴ/ማ/ት/ሥ/ተቋማት የመጀመሪያ ዙር ምልከታ ተደርጎ ለምዘና ጣቢያነት የማያበቃ ተጨማሪ ሥራ እንዲያጠናቅቁ ምክርና ድጋፍ ተሠጥቷቸዋል፣

በኮንስትራክሽን ፣ በኢንዱስትሪያል ፣ በቢዝነስ አገልግሎት እና በሆቴል ቱሪዝም የሙያ መስኮች በ30 የሙያ ዓይነቶች ተመዝጋቢዎች ተጋብዘው 620 ሙያ ብቃት ተመዝጋቢዎች ለምዘና ዝግጁ ተደርጓል፣ ከ20 የመንግስት ቴ/ሙ/ት/ሥ/ተቋማት ከ300 በላይ የሆኑ የB-level መምህራን ለመመዘን የሚፈልጉበትን ሙያ እንዲመርጡ ተደርጎ መረጃው ተጠናቅሯል፣ ለ100000 ሥራ አጥ ወጣቶችና ማህበር በማደራጀት በተለያዩ ሙያዎች የአጫጭር ጊዜ ስልጠና ለመስጠት ከክልሉ ንግድና ኢንዱስትሪ ቢሮ ጋር የስምምነት ውል በመፈራረም ስልጠናውን በየተቋማቱ ለመጀመር ዝግጅት ተደርጓል፣ የሀዋሣ ቴ/ሙ/ት/ሥ/ኮሌጅ የISO ሰርተፊኬት ለማግኘት ከሚሠራው ሥራ አንፃር ለድጋፍ ሠጪ ሰራተኞች በ“Procedures Work Instructions” እንዲሁም ሪከርድና ዶክመንት አያያዝና ልዩ ልዩ ቅፃቅጾች አጠቃቀም ላይ ስልጠና የማስተባበር ሥራ ተሠርቷል። በተለያዩ ሙያዎች ተጀምሮ የነበረው የትብብር ሥልጠና ሲከታተሉ የነበሩ 683 ሠልጣኞች በየሩብ ዓመቱ ሥልጠናውን አጠናቅቀዋል።

የምህንድስና አቅም ግንባታ ሥራዎችን በባለድርሻ አካላት ዘንድ ታውቆ ተገቢው ሥራ ማከናወን እንዲቻል በየሴክተሩ ካሉት ፈፃሚዎች የተውጣጣ ቴክኒካል ቡድን /Team/ እንዲቋቋም ተደርጓል።
ለተቋቋመው ቴክኒካል ቡድን ሥራውን አስመልክቶ በእሴት ሰንሰለት አሠራር ዙሪያ ለአንድ ቀን ሥልጠና እንዲሰጥ ተደርጓል። ስልጠናው በክልሉ ምህንድስና አቅም ግንባታ ፕሮግራምና ፌዴራል የእሴት ሰንሰለት ባለሙያዎች በተገኙበት የተሰጠ ሲሆን፤ በስልጠናው የተካፈሉት አባላት ከግብርናና ገጠር ልማት ቢሮ፣ ከእርሻ ምርት ግብይት፣ ኤክስቴንሽን፣ ከተፈጥሮ ሀብት የሥራ ሂደት/፣ ከቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና እና ከእርሻ ምርምር ተቋም ለተውጣጡ ባለሙያዎች በዝንጅብል ምርት ጥራትና ከቀርከሃ በሚገኙ የምርት ውጤቶች ላይ የሚደረገውን ጥራት አስመልክቶ ሥልጠና ተሰጥቷል።

የግሉን ክፍለ ኢኮኖሚ ከማሳደግ አኳያ የአርሶ አደሩን የግብርና ውጤቶች ከገበያ ጋር ለማስተሳሰር በሚደረገው ሥራ የሁላ /ሀገረሠላም/ ወረዳ የሚገኘውን የቀርከሃ ምርት ከዘመናዊ መንገድ በፋብሪካ ደረጃ ለሚያመርት ከአዳል ፋብሪካ ጋር የስምምነት ውል እንዲፈራረሙ ተደርጓል።

በስምምነቱ ውል የምህድስና አቅም ግንባታ እንደ የቅድመ ምርት ማምረቻ ማሽን እና አዳል ፋብሪካ ሁለት ማሽኖችን በሀገረሠላም እንዲተክሉ ሲደረግ ከሙከራ ሥራና ከሥልጠና ጊዜ በኋላ በምህድስና አቅም ግንባታ ኘሮግራም የተገዛው ማሽን በቀጥታ ለህብረት ሥራ ማህበራት እንዲዛወር ይደረጋል፡፡ በዚህም ወደፊት የህብረት ሥራ ማህበራት የቅድመ ምርት ማምረቻ ሥራውን በራሣቸው እንዲያከናወኑ ይደረጋል፡፡

በክልሉ የዕሴት ሰንሰለት ሥራ ከተጀመረባቸው ዘርፎች አንዱ የዝንጅብል ምርት የሚታየውን የምርት ጥራት ችግር ለመቅረፍ እንዲቻል ከሀዋሣ ግብርና ኮሌጅ አንድ አማካሪ ስልጠና እንዲሰጡ የውል ስምምነት ተፈጽሟል፡፡ ስልጠናው በስድስት ወረዳዎች ማለት ቦሎሶ ሶሬ፣ ቦሎሶ ቦንቤ፣ አደሮ ጡንጦ፣ ቃጫ ቢራ፣ ም/ባድዋቾና ጠንባሮ የሚገኙ 48 ባለሙያዎች ስልጠናውን እንዲካፈሉ ተወስኗል፡፡

## 6. ?? ?? ?? ?? ?? ?? ?? ?? ???? ?

**መ**ንግስት የኢንፎርሜሽን ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂ (ኢኮቴ) በክልሉ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ልማትን ለማፋጠንም ሆነ ራሱን እንደ አንድ ኢንዱስትሪ በማጎልበት የልማት አስተዋጽኦ እንዲያበረክት አስፈላጊውን ድጋፍ እየሰጠ ይገኛል፡፡ በሪፖርቱ **ውስጥ** መሰረታዊ **የ**ኮምፒውተር ስልጠና፣ **የ**ኔትወርክ ዝርጋታ **የ**ድረ-ገጽ ዝግጅት፣ **የ**ጥገና፣ **የ**ቪዲዮ ኮንፈርንስና **የ**ኢንተርኔት **አጠቃቀምና የቴክኒክ** የድጋፍ ሥራዎች ላይ ትኩረት በማድረግ የተከናወኑ **ሲሆን ዝርዝሩ እንደሚከተለው ይቀርባል፡፡**

1.**መሠረታዊ የኮምፒዩተር** ስልጠና ፡-

የክልሉ ኢኮቴ ኤጄንሲ ከክልል እስከ ወረዳ ባሉት መዋቅሮች ለተመለመሉ 80 ከፍተኛ ባለሙያዎች በአድቫንስድ ስልጠናና ለ2500 ባለሙያዎችና አመራሮች በመሰረታዊ የኮምፒተር ክህሎት ለማሰልጠን ግብ ጥሎ የተንቀሳቀሰ ሲሆን በግማሽ ዓመቱ 10 ፈጻሚዎች በሁለት ዙር በኔትወርክ ሰኩሪቲ እና በአድቫንስድ ኮምፒውተር ፕሮግራሚንግ በአዲስ አበባ ስልጠና ወስደው በመመለስ በኔትወርክ ሱኩሪቲና በአድቫንስድ ኮምፒውተር ፕሮግራሚንግ 33 ባለሙያዎች የአንድ የአንድ ሳምንት

የዕውቀት ሽግግር ስልጠና በመስጠት ባለሙያዎች የእርስ በእርስ መማማር ግንዛቤና ክህሎታቸውን ያሳደጉ ሲሆን የቢሮአችንን Network ይበልጥ የተቀናጀና ደህንነቱ የተጠበቀ እንዲሆንና በሰርቨር የተደገፈና ደህንነቱን መከታተል በሚቻልበት ሁኔታ እንዲሰጠር ISA Server በመጫንና ኮንፌገር በማድረግ የኔትወርክ አጠቃቀሙ የተሻለ እንዲሆን ማስቻልና ያለው ኔትወርክም ደህንነቱ የተጠበቀ እንዲሆን ተደርጓል፡፡ ወደ ኔትወርኩ የሚገቡና የሚወጡ የትራፊክ ፍሰቶች መከታተልና አስፈላጊ እርምጃ መውሰድ የሚቻልበት ሁኔታ ተመቻችቷል፡፡ DHCP Configure በመደረጉ ያሉት ኮምፒውተሮች በቀላሉ ከሰርቨሩ IP Address በመውሰድ ወደ ኔትወርክ እንዲቀላቀሉ አስችሏል፡፡ Active Directory Configure በማድረግ እና የተለያዩ ግሩፖች በመፍጠር ሁሉንም የኔትወርክ ተጠቃሚዎች በማዕከል ለመቆጣጠር ያሚያስችል ቅድመ ሁኔታዎች ተመቻችቷል::

ከዚህም ሌላ እስከ አሁን በደረሰን ሪፖረት በክልል ደረጃ 736፤በዞንና በወረዳዎች 1688፤በማህረሰብ የኮምፒተር ማእከላት 809 በጥቅሉ 3233 የመንግስት ሠራተኞች የህብረተሰብ ክፍሎችና አመራሮች የመሰረታዊ ኮምፒውተር ስልጠና ወስደዋል፡፡ ይህ በመሆኑም በወረዳ፣ በዞን እና በክልል የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች የኢኮቴ መሣሪያዎች አጠቃቀምና አያያዝ በከፍተኛ ሁኔታ መሻሻሉን ከሚቀርቡ ሪፖርቶች መረዳት ተችሏል፡፡

በተጨማሪም በአገር አቀፍ ደረጃ በኢኮቴ የግል ዘርፉን ለማስፋፋት በአራቱ ክልሎች የተጀመረውን ኢኮቴ ቢዝነስ ኢንኩብሽን ማእከል ለማጠናከርና የዘርፉን ልማታዊ ሃይል በስፋት ለመፍጠር የሚያስችል የኢኮቴ ኢንተርፕሪነርሽፕ ሰልጠና ከተለየየ ሴክተሮች የተመለመሉ 20 ባለሙያዎች በባህርዳር ለአንድ ሳምንት በኢኮቴ ኢንተርፕሬነርሽፕ ሰልጥነዋል:: ባለሙያዎቹ ከቀሰሙት ትምህርት በመነሳትም በክልላችን ለተቋቋመዉ የደቡብ ኢኮቴ የግል ሥራ ፈጠራ ማስፋፊያ ማዕከል የሚለካ ሙያዊና አስተዳደራዊ ድጋፍ አድርገዋል፡፡ በማድረግም ላይ ናቸው:: ከላይ በተጠቀሰው ስልጠና ውስጥ በክልላችን ግብርና ቢሮ የምግብ ዋስትና አሠራራቸዉን ለማሻሻልና ግንኙነታቸዉን በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የተደገፈ ለማድረግ

በተዘጋጀ ሶፍዌር (Payroll and attendance system software (PASS) ላይ ከክልሉ፣ከዞንና ከወረዳ ለተመለመሉ 512 የየደረጃው ሴፍቲኔት ሰራተኞች በሶፍትዌሩ አጠቃቀምና አያያዝ ለአንድ ወር ተኩል ስልጠና ተሰጥቷል፡፡

የዚህ ስልጠና በኃላ የምግብ ዋስትና ፕሮግራም ተጠቃሚዎችን መረጃ በወቅቱ ለሚመለከተዉ ክፍል ማድረስና በክፍያ ሠነድ ላይ የሚታየዉን አንዳንድ የተዛባ የመረጃ አያያዝን በማስተካከል የአገልግሎት ተጠቃሚዎችን እና በምግብ ዋስትና ሥራ ላይ ለተሠማሩ የማህበረሰቡ ክፍሎች ትክክለኛ የክፊያ ሥርዓት እንዲኖር በማድረግ የምግብ ዋስትና ፕሮግራም አሠራርና አደረጃጀት ዘመናዊ ሆኖ ተገቢውን ተገልጋይ ተኮር አገልግሎት ቀልጣፋና ውጠታማ በሆነ መንገድ መስጠት እንዲችል በማድረግ መልካም አስተዳደር መስፈንና ፈጣነ ልማት ለማስመዝገብ ቴክኖሎጂው ያለው ድርሻ ለማሳየት ተችሏል፡፡

2. ድረ-ገጽ ዝግጅትና አጠቃቀም

የክልላችን አመራር አካለትና ባለሙያዎችና ማንኛውም በአገር ውስጥም ሆነ በየትኛውም የአለም ክፍል የሚገኝ ጠቃሚና ወቅታዊ መረጃዎችን እንዲያገኙና እንዲጠቀሙበት ኤጀንሲው በየደረጃው የሚገኝ የመንግስት መዋቅር ተጠቃሚ እንዲሆን በአመቱ ለ40 ተቋማት ለመስራት ግብ ጥሎ በመንቀሳቀስ በክልል ደረጃ የ21 ተቀማትን ሰርቶ በማጠናቀቅ አስችሏል፡፡

አገልግሎትን ያገኙ የክልል ቢሮዎች፡- ለውኃ ሥራዎች ድርጅት፣ ለሥራ አመራር ተቋም፣ ለብዙሃን መገናኛ ድርጅት፣ ለፀረ-ሙስና ኮሚሽን፣ወጣቶች ቢሮ፣ ለአርብቶ አደር ቢሮ(በሂደት ላይ ያለ፣ክልል ርእሰ መስተዳድር ፅ/ቤትና ሲቪል ሰርቪስ ኤጀንሲ ሲሆኑ ዞን አ/ግንባታ መምሪያዎች ሲዳማ፣ ደቡብ ኦሞ፣ ስልጤ፣ ዳውሮ፣ ጋሞጎፋ፣ ወላይታ፣ ሸካ፣ ጉራጌ እና ከ/ጣምባሮ ዞን" ከልዩ ወረዳዎች፤ ደራሼ ልዩ ወረዳ፣ አማሮ ልዩ ወረዳና የም ልዩ ወረዳሲሆኑ የድረ-ገጽ ሥራው ተጠናቆ በአየር ላይ ውሏል:: በዚህም ተቋማቱ የተሻለ የመረጃ ልውውጥ ተግባራት በማከናወን ላይ ይገኛሉ:: ስራው በባለሙያ ግምት በገንዘብ ሲተመን በአጠቃላይ 231000ብር(ሁለት መቶ ሰላሳ አንድ ሺህ ብር) ይገመታል::

## 3.የኔትወርክ ዝርጋታ ሥራዎች

የኢኮቴ ኤጀነሲ በአመቱ ለማከናወን የ40 ሴክተር መ/ቤቶችና ተቋማት የመረጃ መረብ ዝርጋታ ግብ ጥሎ በመንቀሳቀስ የአካባቢ መረጃ መረብ ዝርጋታ (LAN) ስራ ተከናዉነዋል፡፡ በዚሁ መሰረት በገቢዎች ቢሮ በየደረጃዉ የሚገኙ ጽ/ቤቶች ገቢን ለማሳባሰብና መረጃዎችን መለዋወጥ እንዲችሉ በሃያ ሁለቱ 22ቱም የሪፎርም ከተሞች የመረጃ መረብ ዘርግቶ በመጠቀም ላይ ናቸው፡፡ በሌሎች ዘጠኝ የሴክተር ቢሮዎች፤ ጽ/ቤቶችና የማህበረሰብ መረጃ ማእከሎች እናበ4 ዞኖች (በስልጠ 3፣በወላይታ 2፣በጉራጌ 6 እና በከምባታጠምባሮ ዞን 1)በጥቅሉ የ12 ሰክተር ቢሮዎች የአካባቢ መረጃ መረብ የተዘረጋ ሲሆን በአጠቃላይ በግማሽ አመቱ በክልሉ 43 የአካባቢ መረጃ መረብ ስራ ተከናውኖ ተግባራዊ ሆኗል::

ዝርዝራቸውም የሚከተለው ነው::

1) ክልል ፖሊስ ኮሚሽን
2) ፀረ-ሙስና ኮሚሽን
3) ሲቪል ሰርቪስ ኤጀንሲ(የማስፋፋት ሥራ)
4) 196 ኖድ ያለው የግብርና ቢሮ
5) 50 ኖድ ያለው ፕሬዝዳንት ጽ/ቤት
6) 50 ኖድ ያለው የወጣቶችና ስፓርት ቢሮ
7) የፍትህ ቢሮ የኔትወርክ ዲዛይንና ቅድመ ዝርጋታ ሥራ
8) በ 22 የክልል ሪፎርም ከተሞች ገቢዎች ጽ/ቤቶች እና
9) በፌደራል አይ ሲ ቱ ኤጀንሲ ለተቋቋሙ ለዳሰነችና ሳውላ የማህበረሰብ መረጃ ማእከላት የኔትወርክ ዝርጋታ ክንውኖች ናቸው፡፡ በመሆኑም የኔትወርክ ዝርጋታ ስራችን በገንዘብ ሲተመን ብር 1061151 በላይ ይገመታል::

**4.የተለያዩ የኢኮቴ መሳሪያዎች ጥገና ፣**

በሥራ ክፍሉ ከተለያዩ መ/ቤቶች ፣ ዞኖችና ወረዳዎች ተበላሽተው የመጡና ባለሙያዎች በአካል በክልል መ/በቶች፡ በዞኖችና በልዩ ወረዳዎች ተገኝተዉ የጥገና አገልግሎት ሠጥተዋል፡፡ በዞኖችና በልዩ ወረዳዎች የሚገኙ ባለሙያዎችም በየስራ ምድባቸው የተለያዩ መለስተኛ ጥገናዎችን አከናውነዋል:: ከዚህ አንጻር ኤጀንሲው በአመቱ 150 የተለያዩ የኢኮቴ መሳሪያዎችን ከክልል እስከ ወረዳ ባሉ ባለሙያዎች ለመጠገን አቅዶ በግማሽ አመቱ 196 በክልልና 964 ልዩ ልዩ መሳሪያዎች በዞኖችና በወረዳዎች በጥቅሉ 1160 የተለያዩ መሳሪያዎችን በመጠገን ከብር 186030 በላይ የመንግስት ወጪ ከማዳኑም በተጨማሪ መሳሪያዎቹ በወቅቱ ተጠግነው አገልግሎት እንዲሰጡ ተደርገል:: ይህ ተግባር በየደረጃዉ በተለያዩ መንዶችና በተዘዋዋሪ የምባክነዉን የመንግሥት ንብረትና ገንዘብ በከፍተኛ ደረጃ ለመቆጠብና ለማስተዳደር ተችላል፡፡ በዕዉቀትና በግንዛቤ ማነስ የተነሣ ወድቀዉ ይቀሩ የነበሩ የመንግሥት ኢኮቴ ንበረቶች ትኩረት አግኝተዉ ከጥፋት ድነዋል፡፡ በመሆኑም ቢሮዎችና ጽ/ቤቶች የተጠገኑ ንብረታቸዉን በወቅቱ ባጠረ ጊዜ ተረክበዉ ሥራቸዉን እያከናወኑ ይገኛሉ፡፡ ወደፊትም የሚቀጥል ይሆናል፡፡ ዝርዝሩን በአባሪ ሁለት ይመልከቱ፣

## 5. ተቋማት የሚገዙ የአይሲት ዕቃዎችን ስታንዳርድ ለማስጠበቅ የተደረገ ዝርዝር መለኪያ ዝግጅት

ዝርዝር መለኪያ ማዘጋጀትና የተገዙ ንብረቶችን በዝርዝር መለኪያዎች መሠረት መርምሮ ለመረከብ፡ በተለያዩ መነሻዎች የሚዛቡ አሠራሮችን ለማስተካከልና የሚጭበረበሩና ደረጃውን ያልጠበቀ የግዥ ሂደቶችን በማረም ለሥነ-ምግባርና ፀረሙስና ትግላችን ከፍተኛ አስተዋፅዖ ከማበርከቱም በላይ የአይሲቲ መሳሪያዎች ለኤጀንሲው (ፌዴራል) የተዘጋጁ ስታንዳርዶችን በማስጠበቅ በኩል ከፍተኛ ድርሻ አለው፡፡ በመሆኑም የዚህ አገልግሎት ተጠቃሚ የሆኑ ቢሮዎች፣ ጽ/ቤቶችና የባለሥልጣን መ/ቤቶች ፍላጎታቸዉን መሠረት ያደረጉ ዝርዝር መለኪያዎች ተሠርቶ

የተሠጣቸዉ ሲሆን መለኪያ ዝርዝሩን እያሚሉ ግዥው እንዲፈፀም የተደረገ ሲሆን ያልተሟላው እንዲመለስ በማድረግ የመንግሥት ንብረትና ሃብት በአግባቡ ለማስተዳደር ችለዋል። በመሆኑም የክልል ምክር ቤት 33 ኮምፒውተሮችና 42 ፕሪንተሮች ፣ ግብርናና ገጠር ልማት ቢሮ 40-ኮምፒውተሮችና 5 ላፕቶፖች ፣የወጣቶችና ስፖርት ቢሮ 2 ላፕቶፖችና 12 ዴስክቶፕ ኮምፒውተሮች ፣የገቢዎች ባለስልጣን 1 serverስ እና የሥራ አመራር ተቋም የገዟአው እቃዎች የቴክኒክ ምርመራ ተደረጉላቸው ተቋሚቱ እንዲረከቡ ተደርጓል። እነዚህ ተግባራት በገበያ ዋጋ  በባለሙያ ግምት ወጪያቸው በቀላሉ የአንዱ ዋጋ 100 ብር በአማካይ ሲታይ 13500ብር ይሆናል።

6. ቪዲዮ ኮንፍራንስና የኢንተርነት  አጠቃቀምና አገልግሎት

- አገራችን በአዲሱ የመረጃና የመገናኛ ቴክኖሎጂ የVideo conferencing አገልግሎት በስፋትና በጥልቀት ተጠቃሚ ስትሆን በአፍሪካ ግንባር ቀደም አገር ናት። በመሆኑም ለክልላችን ማህብራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ጠቀሜታ በአጠቃላይና ለድህነት ቅነሳና ለፀረ-ሙስና ትግል በተናጠል የሚያበረክተዉ ጠቀሜታ የጎላ ነዉ።

- ለርዕሰ መስተዳድር ጽ/ቤት - 4 ጊዜ - 10 ሰዎች ለ4ቀን  በጥቅሉ ለ40 ኃላፊዎች
- ለትምህርት ቢሮ - 2 ጊዜ - ለ3000 ተሳታፊዎች ለ20 ቀን 2 ጊዜ በጥቅሉ ለ6000 ተሳታፊዎች
- ለከተማ ልማት ቢሮ - 2 ጊዜ - ለ5 ሰዎች ለ1 ቀን  በጥቅሉ ለ 10 ሰዎች
- ለሰቶች ጉዳይ 2 ጊዜ 5 ሰዎች  ለ2 ቀን
- ለክልል ት/ቢሮ 62000 ተሳተፊዎች 1 ጊዜ ለ15 ቀን
- ለክልል አ/ግ/ቢሮ 72000 ተሳቲፊ ዎች ለአንድ ጊዘ ለ8 ቀናት

ለጋምቤላ ክልል 600 ተሳታፊዎች ለ1 ጊዜ ለ1 ቀን ሆኖ በአጠቃላይ ለ134645 ተጠቃሚዎች በአማካይ ለ4 ቀናት በክልል ደረጃ አገልግሎት ተሰጥቷል፡፡ በዚሁ መሰረት በግማሽ ዓመቱ 70 ሚሊዮን ብር ከወጪ ማዳን ተችሏል።

ይህ የሚያመለክተው፡- ICT ለድህነት ቅነሳው ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታው ከፍተኛ መሆኑን፣ መልክዕክቱን በፍጥነት ሁሉም በያለበት ተደራሽ ባድረጉን፣ከመልካም አስተዳደር አንጻር ሰልጣኙ ባለበት ሆኖ በተገልጋዩ ተገቢውን አገልግሎት መስጠት መቻሉና በአበል፣ በነዳጅ ወዘተ...የሚወጣ አላስፈላጊ ወጪን በመቀነስ ግልጽነት

ማስፈኑንና ቴክኖሎጂውን ማስተዋወቅና ዘመናዊነትን ማምጣቱን በመሆኑ የበለጠ ትኩረት ሊሰጠው ይገባል፡፡

7. **የኢኮቴ መሰረተ ልማት ስርጭት መርጃ ማሰባሰብ ሥራ**

የኢኮቴ መሰረተ ልማቶች ክልላዊ ስርጭት በትክክልና በተገቢው መንገድ ለማወቅ በተደረገ ጥረት በክልሉ ወረዳዎች ከተማ አስተዳደርና ሴክተሮች የሚገኙና ለመልካም አስተዳደር መስፈን ድርሻ ያላቸው የቴክኖሎጂዊ መረጃዎች የተሰባሰበ ሲሆን በ2ኛ የሩብ ዓመት የተሠራጩትን ጨምሮ በሚከተለዉ መልኩ ይታያል።

በክልሉ ሴክተር መ/ቤቶችን ሳይጨመር በዞንና ወረዳዎች የተሰባሰበው መረጃ እንደሚያሳየው ኮምፒውተር፣ ኘሪንተር፣ የፋክስ፣ ስካነር ያላቸው መሆኑንና በአንድ ወረዳ ምንም አይነት ኮምፒተርና ተዛማጅ እቃዎች እንደሌለው ለመረዳት ተችሏል፡፡ በዝርዝር ሲታይ :-

1. የኮምፒውተር ብዛትን በተመለከት 10161 ሆኖ ከፍተኛው 87 በጨንቻ ወረዳ ዝቅተኛው ደግሞ 0 በጭሪ ወረዳ መኖሩ ተረጋግጧል፡፡
2. የኘሪንተር ብዛት 2956 ሆኖ ከፍተኛው 42 በየም ልዩ ወረዳ ዝቅተኛው ደግሞ 0 በጭሪ ወረዳ ይገኛል።
3. የፋክስ ብዛት 1004 ሆኖ ከፍተኛዉ 12 በኮንሶ ወረዳ ዝቅተኛው 0 በጭሪ ወረዳ እንደሚገኘ ተረጋግጧል።
4. ስካነር ብዛት 1867 ሆኖ ከፍተኛው 12 በኪንዶ ዲዳዬ ወረዳ ዝቅተኛው 0 በጉራፈርዳና በጭሪ ወረዳ መኖሩን።

ይህ በየሴክተሩ የሚለያይ ሲሆን በአንዳንድ ዞኖች የሴክተሮችን የከተማ አስተዳደሮችንና የምክር ቤቶችን ሳያካትቱ መላካቸው ተረጋግጧል። በክልል ሴክተሮችም ሙሉ በሙሉ አልተሰባሰበም ስለሆነም የማጣራት ሥራ በመከናወን ላይ ነዉ። የዚህ መረጃ ማሰባሰብን በተመለከተ አገሬቱ ኤኮቴን የድህነት መቅረፍያ መሳሪያ መሆኑን በመገንዘብ በሁሉም ተቋማት E-government ተግባራዊ ለማድረግ ተመጣጣኝ የሆነ አገልግሎት ለመስጠት ጊዜ ያለፈባቸውን መሳሪያዎች በሌላ ለመተካት ደረጃውን የጠበቀ አገልግሎት የሚሰጡ መሳሪያዎች ለመትከል ቁልፍ የኢኮኖሚ ሴክተሮችን

በመለየት እንደቅደም ተከተሉ ጥቅም ላይ ለማዋልና በየዓመቱ የሚያስፈልገውን ያህል በዕቅድ ይዞ ለሚሟላት ነው።

ሽቦ አልባ ስልክን በተመለከት በክልሉ በ113 ወረዳዎች በሚገኙ የተለያዩ ቀበሌዎች፡ መንግስታዊ ተቋማትና መነግስታዊ ባልሆኑ ተቋማት በጥቅሉ የተሰራጨ 2553 የሽቦ አልባ ስልክ የሚገኙ ሲሆን የክልሉ 21 ወረዳዎች ውስጥ የሚገኙ የገጠር ቀበሌዎች ደግሞ ስርጭቱን ያላገኙ መሆኑን ማረጋገጥ ተችሏል። 1975 የገጠር ቀበሌዎች ስርጭት ያላቸው ሲሆን 54% የክልሉ የገጠር ቀበሌዎች ህዝብ ተጠቃሚ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ ከነዚህ ውስጥም 1755 የሚሰሩ ሲሆን በተለያዩ ወረዳዎችና ቀበሌዎች 206ቱ አይሰሩም። ከ 6 በላይ የሚሆኑትም በስርቆት መጥፋታቸዉ ከጉራገና ከጋሞጎፋ ዞኖች ሪፖርት ተደርጓል። ከነዚህ ውስጥ 97ቱ ተጠግነው አገልግሎት መስጠት ከተዘረጉት ሽቦ አልባ ስልኮች ውስጥ 79% በገጠር ወረዳዎች 13% በመንግስት መ/ቤቶች 6% በግል ተቋማት እና 2% በNGO ነው፡፡

በክልሉ የመደበኛ ስልክ ስርጭት 75858 ሲሆን የባስኬቶ ልዩ ወረዳ መረጃ ስላልደረሰ አልተካተተም፡፡ Fixed telephone density 0.025% መሆኑን ያሳያል፡፡
ሞባይል ስልክ ስርጭት ደግሞ 66643 ሰሆን (ሸካ ዞን፤ የም፤ አማሮ፤ ባስኬቶና አላባ) ልዩ ወረዳን መረጃ ከ6 ጊዜ በላይ ተጠይቀው ሊሰጡን ባለመላካቸው አልተካተተም፡፡

የመንግሰት ፖሊስና ስትራቴጂ ተቀርጾ የገጠሩ ሕዝብ የመረጃ መረብ ተጠቃሚነት እንዲረጋገጥ በየጊዜው የሚታቀደው ተግባራዊ መሆን አለመሆኑንና የክልሉን የልማት ሥራ በማፋጠን በኩል ያለውን ድርሻ ለመለየትና ቀሪ ክልላዊ የቴክኖሎጂውን የስርጭት ድርሻ ከሚመለከተዉ አካል ጋር በመነጋገር በዕቅድ ተይዞ እንዲፈጸም ለማድረግና የቴክኖሎጂው ክልላዊ ስርጭት ፍትሃዊ ሆኖ የእኩል ተጠቃሚነት መርህን ለመተግበርም ሆነ ክልሉ የተያያዘውን የልማትና የመልካም አስተዳደር መስፈን ክልላዊ ተግባርን ለመፈጸም ዘርፉ ያለው ድርሻ የላቀ በመሆኑ በየአንዳንዱ ዞኖች ለመረጃው ያላው ትኩረት ሊሰጠው ይገባል፡፡ ሆኖም የዚህ ስርጭት ዴንሲቲ ሲታይም 0.06% ብቻ መሆኑን ያሳያል፡፡

## 8. የማህበረሰብ መረጃ ማዕከል አገልግሎትና ስርጭት

መንግስት ልዩ ትኩረት ሰጥቶ ከሚያከናዉናቸዉ መጠነ ሰፊ የዘርፉ እንቅስቃሴዎች በተጓዳኝ ከአበዳሪና ረጂ ድርጅቶች ጋር በሚያደርገው የሁለትዮሽ ግንኙነት የክልላችን የኢኮቴ ኤጀንሲ መልካም ልምድ አለው፤፤ይህንን ግንኙነት መሰረት በማድረግ የዘርፉ የሥራ ሂደት በክልሉ  የተለያዩ ዞኖችና ወረዳዎች 24 የማህበረሰብ መረጃ ማዕከላት የተቋቋሙ ሲሆኑ በዓመቱ  ከፌዴራሉ ኤጄንሲ ጋር በመተባበር 6 የማህበረሰብ መረጃ ማዕከላት ለማቋቋም አቅዶ በ6 ወሩ 6 ማዕከላት (በሳውላ" በጂንካ" ዳሰነች" በሾኔ" በክልል ወጣቶች ማዕከል እና በይርጋአለም) አቋቁሞ  ወደ ተግባር አሸጋግሯል፡፡

እነዚህ ማዕከላት በተለያዩ ሁኔታ የኢኒቴርኔት፣የፋክስ፣ የፎቶኮፒ፣ የስልክ አገልግሎትና  መሰረታዊ  የኮምፒተር ስልጠና በመስጠት ላይ ይገኛሉ። በርካታ ወጣቶችና ማህበራትንም ተጠቃሚ በማድረግ ላይ ይገኛሉ። የዚህ ዘርፍ ዋና ዓላማን በተመለከተ ሁሉም የአገራችን 15000 ቀበሌዎችና የክልላችን 3661 (በሃገራዊ ሴንሰስ በተቀመጠው መሰረት ቀበሌዎችና ነዋሪዎች በአጭር ጊዜ የቴክኖሎጂውን እውቀት ጨብጠው ለፈጣን ልማት ትግላችን የበኩላቸውን ድርሻ እንዲያበረክቱ ማድረግ ነው፡ ይህ ደግሞ በመንግስት ብቻ የሚቻል ባለመሆኑ መንግስት ከረጂና አበዳሪ ድርጅቶች ጋር በመተባበር የግል ባለአብቶች በዘርፉ እንዲሰማሩ ማድረግ የብዙሃን ድርጅቶችን በማደራጀትና በማሰልጠን ባለቤት ሆነው የዘርፉን ሥራ በሕጋዊነት እንዲያስፋፉት ማድረግ፣ ወጣቶች ወደ ቴክኖሎጂ ቀርበው ተጠቃሚ እንዲሆኑ በዚህም ሥራ አጥነት እንዲቀረፉ ማድረግ ሆኖ ለኢኮኖሚ ልማቱና ለመልካም አስተዳደር ድርሻቸውን እንዲያበረክቱ ነው::

ይሁን እንጂ ማዕከላቱ በተቋቋሙባቸው መስተዳድሮች የተወሰኑ አመራሮቻችንና መዋቅሮቻችን እራሳቸው አካል አደርገው የመከታተል የመቆጣጠርና የመደገፍ ችግር አለባቸው:: አብዛኞቹ በተገቢው በመመራታቸው ያልተጠበቀ ውጤት በማሳየት ላይ የሚገኙ ሲሆን ( ጎንቸሬ፣ ይርጋዓለም፣ ከምባ፣ ዳውሮ፣ ዲላ፣ ጂንካ፣ በዴሳ እና ዱራሜ ወዘተ) ሌሎች ደግሞ ( ስልጤ፣ ጉራጌ፣ (ወልቂጤ)፣ ሀዲያ(ሀዲያ ከተማ አስተዳደር)፣ ሲዳማ (ቦና ወረዳ) ፣ ከፋ(ቦንጋ ከተማ)፣ ደቡብ ሆሞ ዳሰነች) ፣ ኮምፒውተሮችን ከተዘረጋው የመረጃ መረብ በመነቃቀል ሰርቶ ማስቀመጥ፣ ላልተፈቀደለት አገልግሎት

ማሰራጨትና አገልግሎቱን ተገልጋዩ እንዳይጠቀሙበት ሲደረግ ያለማስተካከል፣ ዕቃዎችና ለማዕከሉ የሚላኩ ገንዘቦች ሲሰረቁ፣ ሲዘረፉና ዘራፊዎችም ሲሰወሩ ተከታትሎ ሕጋዊ ርምጃ በመውሰድ ረገድ ድጋፍ ያለማድረግ፣ አንዳንዶቹም ሁሉ ነገር ተሟልቶ ግማሽ ሚሊዮን የሚደርስ ገንዘብ ተልኮ ያለአገልግሎት ሲቀመጥ ያለማስተካከል። በዚህም ምክንያት ረጂ ድርጅቶች በተለያየ መንገድ አረጋግጠው ለመርዳት ያለመፈለግ ሁኔታ ተፈጥሯል።

9.የደቡብ ኢኮቴ **የግል *ሥራ ፈጠራ ማስፋፊያ* ማዕከል**( **SICT Busines incabution center)**

በአሁኑ ጊዜ የኢኮተ ሙያ ተመራቂዎች ከትንሹ ሰርተፍኬት እስከ ዲግሪ በክልሉ መንግስታዊና መንግስታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች በብዛት እየተፈጠረ ይገኛል፡፡ በፌዴራል ደረጃም በተለያዩ ዩኒቨርስቲና ኮሌጆች በተመሳሳይ ሁኔታ እየተፈጠሩ የሚገኙ ሲሆን እነዚህ ባለሙያዎች ከተቀጣሪነት አልፈው በግል የሙያው ዘርፍ ሥራ ፈጣሪ ሆነው ተገቢውን ሃገራዊ የዜግነት ድርሻ እንዲወጡ ለማድረግ የሚያስችል ማዕከል በ4 ክልሎች እንዲቋቋም ዕቅድ የነበረ ቢሆንም በአፈጻጸሙ ግልጽነት መጓደል በክልላችን ሳይቋቋም ቆይቶ የነበረው በአሁኑ ጊዜ ተቋቁሞና ተቋሚዊ መሰረቱ ተደራጅቶ ሥራውን የጀመረ ሲሆን በክልሉ በአካል በመንቀሳቀስ ከዞን የአቅም ግንባታ መዋቅሮች ጋር በተፈጠረ መስተጋብር በዓለም ባንክ ከተፈቀደለት 6 ካምፓኒዎች የማፍራት ዕቅድ በላይ 48 ካምፓኒዎች በማግኘት የተመረጡና ውጤታማ የሆኑትን 12 ካምፓኒዎች ወደ ተግባር በማስገባት መደበኛ ሥራውን በማከናወን ላይ ይገኛል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በክልሉ አ/ግንባታ ቢሮ ግቢ G+3 የሆነ ህንፃ ከመንግስት ጋር በጋራ እንዲሠራ በተደረሰ ስምምነት በዓለም ባንክና በፌዴራል ኤጀንሲው ድጋፍ የግራውንድ + 1 የግንባታ ሥራ ተጀምሮ የመሠረትና የቢም ሥራ ተጠናቅቋል፡፡ በቀጣይ ሁለት ወር ጊዜ ዉስጥም የተጀመረዉ ግንባታ ይጠናቀቃል።ተብሎ የጠበቃል፡፡ መሰል ቅርንጫፍ ማዕከሎች በ4 የክልሉ አማካኝ ቦታዎች ለመዘርጋት ጥናት በማድረግ ላይ ነው፡፡ ለዚህ የተሳካ ውጤት በግንባር ቀደምትነት ድጋፍ ላደረጋችሁ የዞን

አ/ግ/መምሪያዎችና ሃላፊዎች ምሥጋናችን የላቀ ሲሆን በሁሉም የአይሲቲ ሥራዎች ዘርፍ ተመሳሳይ ድጋፍ ማድረግ ለዕድገታችን ወሳኝ ነው::

## 10.በግ ማሽ አመቱ የተከናወነ የአኮቴ መሳሪዎች ስርጭት

በክልላችን ከ91 በላይ የሥራ ሂደቶች ተጠንተው ወደ ትግበራ የተሸጋገሩ ቢሆንም የቴክኖሎጂ ፍላጎት ጥያቄያቸው ከፍተኛና እልህ አስጨራሽ ተነሳሽነትንና ቁርጠኝነትን የሃብት መጠን ሰፊ አቅምን የሚጠይቅ ነው:: በዚህ መሰረት ኤጀንሲ:: በርካታ ጨረታ አውጥቶ በበጀት እጥረት ተግባራዊ ሊሆኑ ያልቻሉ ቢኖሩም በዓለም ዓቀፍ ጨረታ የተገዙና ገቢ የተደረጉ 500 ኮምፒዩተሮች፣560ፕሪንተሮች፣92 ፋክሶች;402--ዩፕአስና 14 ስካኖሮች ፊትሃዊ በሆነ መንገድ ለ134 ወረዳዎች;22 ከተማ አሰተዳደሮችና ሴክተር መስሪያ በቶች ተሰራጭቷል።

## 11.ድጋፋዊ ክትትልና አቅም ግንባታ

በየደረጃው የሚገኘውን የዘርፉን አከላት ከመደገፍና አቅም ከመገንባት አንፃር በክልል ደረጃ 35 ወረዳዎችንና 35 ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች በመጎብኘት ሙያዊና ቴክኒካዊ ድጋፍ በማድረግ፣ አገልግሎት የማይሰጡ የት/ቤቶች ፕላዝማዎችና፣ የወረዳ ኔቶች ሁሉ አገልግሎት እንዲሰጡ የተደረገ ሲሆን ለክልሉ ፍትህ አካላት ማሰልጠኛ ተቋምና ለኦዲት ቢሮ ፊተና በማዘጋጀትና በመፊተን ፤በ 7 ዞን በሚገኙ ሴክተር መስሪያቤቶች የመሰረታዊ የስራ ሂደት ለውጥ ለተገበሩ ቢሮዎች፤ በከምባታ ጠምባሮ ዞን በሚገኙ አራት ወረዳዎች ድጋፍና ክትትል ሥራ ተሰርቷል፡፡ እንዲሁም በሃዲያ ዞን ሶሮ ወረዳ መስክ የ4 ቱን ችግር የማስተካከል፤ በተለያየና በተደጋጋሚ ጊዜ ወደ 12 የሚጠጉ የክልል ቢሮዎችን በአካል በመሄድ ያጭር ጊዜ የቴክኒክና የሙያ ድጋፍ ተደርጎላቸዋል፤ የክልሉ ፋይናንስ ቢሮን የኢንተርኔት መስመር ችግር ለመፍታት አዲስ አበባ በአካል በመሄድና በመነጋገር ችግሩ እንዲፈታ በማድረግና በክልሉ በሚገኙ የተለያዩ ወረዳዎች ከ15 ጊዜ በላይ በተለያየ ጊዜ በስልክ ድጋፍ ተሰጥተል፣ በዞንና በወረዳ መዋቅሮችም 2 ጊዜ በሁለቱ የሩብ ዓመት ውስጥ ለበርካታ ሴክተሮች ድጋፍ ተደርጓል::

## 7. ያጋጠሙ ችግሮች

1. ለ□·□· ሊያገኝ የሚገባውን ትኩረት አግኝቶ በየደረጃ□· ባለው የአመራር አካላት □□ተመራ አለመሆኑ፣
2. በክልል የሚገኙ ሃላፊዎችና የሥራ ሂደት ባለቤቶች በታችኛ□· እርከን የሚገኙ ሥራ ሂደቶችን □□□□□ እና በአፈፃፀም ላይ ላጋጠሙ ችግሮች መፍትሔ እንዲሰጣቸው ከታችኛ□· እርከን ጥያቄዎች ሲቀርቡ ፈጥኖ የማያዳግም መፍትሔ አለመስጠት
3. ለክትትልና ድጋፍ አፈፃፀም በተዘጋጀው ሰነድ መሠረት ከየካቲት 2001 ጀምሮ የክትትልና ድጋፍ ቲም በየሴክተሩ ተቋቁሞ መከታተል ተገቢ ቢሆንም አንዳንድ ሴክተሮች ቲሙን ያላቋቋሙ፣ አንዳንዶች ቲሞችን አቋቁመው በተሟላ መልኩ ወደተግባር ያላሰማሩ በመሆኑ ስለእንቅስቃሴው ጥንካሬና ድክመት በቂ መረጃ አለመኖር፣
4. የለውጡ ሙሉ ፓኬጅ አለመተግበር ጋር ተያይዞ ፈጻሚዎች ዘንድ የሚቀርብ ከለውጡ ተጠቃሚ ለመሆን የደመወዝና ጥቅማ ጥቅም/ ትምህርት ያሻሻሉ፣ በድልድሉ ወቅት ከዝቅተኛ ደረጃ  ወደ ከፍተኛ ደረጃ የተመደቡ ../ ጥያቄ በመኖሩ ችግሩ አጣዳፊ መፍትሄ ካላገኘ በለውጡ ቀጣይነትና ተነሣሽነት ላይ ችግር እያስከተለ መሆኑ፣
5. እያንዳንዱ የሥራ ሂደት በጥናቱ ወቅት በተቀመጠው ስታንዳርድ መሠረት በየዕለቱ ሥራውን እየላከና መረጃ እየያዘ ከመሥራት አንፃር ሰፊ ክፍተት መኖሩ፣
6. በየአካባቢ የሚገኙ ምርጥ ተሞክሮዎችን በፍጥነት እንዲስፋፉ ሁኔታዎችን ካለማመቻቸቱም  ሌላ የነበሩትም እየተዳከሙ መሄደቸው/ ለምሳሌ በሀዋሳ ከተማ ታቦር ክፍለ ከተማ የነበረው የለውጥ አተገባበር አበረታች ሲሆን በሀዋሳ ከተማ ውስጥ ላሉ ሌሎች ክፍለ ከተሞች እንኳን እንዲስፋፉ ማድረግ ባለመቻል ታቦር ክፍለ ከተማም ጭምር ከበፊቱ አንጻር እየደከመ መሆኑ/፣
7. በየደረጃው የሚገኙ አዳዲስ ሃላፊዎችና በቅጥርም ሆነ በሽግሽግ የተመደቡ ፈፃሚዎች ሥልጠና ያላገኙ በመሆናቸው ከፍተኛ ግንዛቤ ክፍተት መኖሩና በተግበራው አሉታዊ ተፅዕኖ ማሳደሩ፣
8. አንዳንድ ተቋማት ከዚህ በፊት የተጠኑ ሥራ ሂደቶችን በአግባቡ ሳይተገብሩ ወይም መተግበር ሳይጀምሩ ተጨማሪ አዳዲስ የሥራ ሂደቶች እንዲጠኑ ጥያቄ እያቀረቡ

መሆኑ፣

9. መሠረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥ ውጤታማነትን ማረጋገጥ የሚችል ቢሆንም በቅልጥፍና ላይ ብቻ መተኮሩና የግንዛቤ እጥረት መኖሩ፣
10. በተሸከርካሪ እጥረት በተያዘው ዕቅድ መሰረት መሠረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥ ውጤታማ እንዲሆንና የሰክተሩን እቅድ አፈጻጸም ክትትልና ግምገማ ለማድረግ መቸገር፣
11. የዝውውር እገዳ በመነሳቱ መሠረታዊ የሥራ ሂደት ጥናት መሰረት ምደባ የተሰጣቸው ባለሙያዎች ወደሌላ የሥራ ሂደት፣ ሌላ መ/ቤትና ወደ ሌሎች ክልሎች በመዛወር ልምድ ያላቸው ሰራተኞች ማጣት፣
12. አጠቃላይ መሠረታዊ የሥራ ሂደት ትግበራው እንደ ጥናቱ ጊዜ የአመራር ትኩረት አግኝቶ እየተመራ ካለመሆኑ በተጨማሪ ችግር ያለባቸው መ/ቤቶች ላይ የሚወሰድ እርምጃ ደካማ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ መ/ቤቶቹ ማሻሻያ እርምጃ አለመውሰድ ወይም በችግሩ ውስጥ ባሉበት መሆናቸው ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

## 8 በቀጣዩ የዕቅድ ዘመን ትኩረት የሚደረግባቸው ነጥቦች

- ቀበሌያት አገልግሎት አሰጣጣቸውን በተጠናከረና ቀጣይነት ኖሮት ተቋማዊ መዋቅር ይዞ እንዲሰራ የቀበሌ ሥራ አስኪያጆችን አቅም መገንባት፣
- የመሠረታዊ ስራ ሂደት ለውጥ ጥናት ለማሳካትና በተክክል ለመተግበር የተቀናጀ ድጋፍና ክትትል ሥራን ማጠናከር፣
- የተጠናከረ የግንኙነት ስርዓት እንዲይፈጠር የመረጃ አያያዝና ልውውጥ አጠናክሮ መቀጠል፣
- በአርብቶ አደር አካባቢ የመልካም አስተዳደር ፓኬጅን መተግበር፣
- ምርጥ ተሞክሮን በመቀመር ለልምድ መቅሰሚያ ማድረግ፣
- በዐቅድ አፈጻጸም ግምገማ መነሻ የማበረታቻ ሽልማት መስጠት ናቸው፡፡